# በሽብርተኝነት አዋጅ 2000 መሰረት ለታሰሩ ሰዎች የተጻፈ የመብቶች ደብዳቤ

ይህ በራሪ ጽሁፍ በስኮትላንድ ውስጥ በፖሊስ ጣቢያ ቁጥጥር ስር በሚሆኑበት ጊዜ በህጉ መሰረት ስለሚኖሩዎት መብቶች ጠቃሚ መረጃ ይሰጥዎታል። ይህ ሰነድ በእስር ላይ እያሉ ስለሚኖሩዎት መሰረታዊ መብቶች ይነግርዎታል። ይህ ህጋዊ ምክር አይደለም እንዲሁም ስለሚኖርዎት ሁሉም መብቶች አይነግርዎትም። የራስዎን የግል ህጋዊ ምክር መፈለግ አለብዎት።

ይህን መረጃ በተቻለ ፍጥነት ያንብቡት። በፖሊስ ጣቢያ ሳሉ ውሳኔዎችን ለመወሰን ይረዳዎታል። በዚህ በራሪ ጽሁፍ ውስጥ ያልተረዱትን ማንኛውም ነገር፣ ማለትም በቀላሉ የሚያነቡበት ቅጂ ወይም ትርጉም ከፈለጉ፣ እባክዎ እንዲያብራራልዎት ፖሊሱን ይጠይቁ።

**መብቶችዎን ያስታውሱ፦**

- ፖሊስ በምን ምክንያት በቁጥጥር ስር እንዳዋልዎት የማወቅ መብት አልዎት።
- ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ እንደሆኑ ጠበቃዎ እንዲነገረው የማድረግ መብት አልዎት። ይህም ነጻ ነው።
- ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ እንደሆኑ ስለ ደህንነትዎ ለማወቅ ፍላጎት ሊኖረው ለሚችል ሰው እንዲነገረው የማድረግ መብት አልዎት። ለምሳሌ፣ ይህ ሰው የቤተሰብ አባል፣ ተንከባካቢ ወይም ጓደኛ ሊሆን ይችላል።
- ምንም ነገር ያለመናገር መብት አልዎት። ፖሊስ ለሚጠይቅዎት ማንኛውም ጥያቄዎች መልስ የመስጠት ግዴታ የለብዎትም። ነገር ግን ስምዎን፣ አድራሻዎን፣ የልደት ቀንዎን፣ የትውልድ ቦታዎን እንዲሁም የትውልድ ሃገርዎን መረጃ መስጠት አለብዎት።
- ፖሊስ እርስዎን ጥያቄዎችን ከመጠየቁ በፊት ያለ ምንም መዘግየት ለብቻ ሆነው ጠበቃ የማናገር መብት አልዎት። እንዲሁም ፖሊስ እርስዎን ጥያቄዎች በሚጠይቅበት ጊዜ በማንኛውም ሰዓት ጠበቃ የማናገር መብት አልዎት።
- ከ 16 ዓመት በታች፣ ወይም ከ 18 ዓመት በታች ከሆኑ እና በግዴታ የቁጥጥር ትዕዛዝ ስር ተገዢ ከሆኑ፣ በፖሊስ ጣቢያው ውስጥ በወላጆችዎ ወይም አሳዳጊዎ የመጎብኘት መብት አልዎት።
- አስቸኳይ የህክምና እርዳታ የማግኘት መብት አልዎት።
- ፖሊስ እርስዎን ስላስተናገደበት መንገድ ቅሬታ የማቅረብመብት አልዎት።

## መብቶችዎ

እባክዎን ያስታውሱ፡- በልዩ ሁኔታዎች ውስጥ፣ ፖሊስ ከእነዚህ መብቶች መካከል የተወሰኑትን እንዳያገኙ የማድረግ ወይም የማዘግየት መብት አለው። ለምሳሌ፣ የሌላ ሰውን ጉዳት ለማስቆም እርስዎን ማናገር እንዳለበት ፖሊሱ የሚያስብ ከሆነ። **ይህ የእርስዎን ምንም ያለመናገር መብት አያካትትም።**

## 1. በፖሊስ ቁጥጥር ስር ስላሉ ሰዎች የሚሰጥ መረጃ

- **ለምን በቁጥጥር ስር እንደዋሉ እና እንደታሰሩ የማወቅ**

ለምን በቁጥጥር ስር እንደዋሉ እና ለምን በሽብርተኝነት ተልዕኮ፣ ዝግጅት ወይም አነሳሽነት እንደተጠረጠሩ መረዳት እንዲችሉ ፖሊስ መረጃ ሊሰጥዎ ይገባል።

በፖሊስ ጣቢያው ውስጥ፣ ፖሊስ ለምን መታሰር አለብዎት ብሎ እንዳመነ ሊነግርዎት ይገባል።
በሽብር ተግባር ውስጥ ተሳትፈዋል ተብለው ስለተጠረጠሩበት ነገር ማናቸውም ጥያቄዎች ከመጠየቅዎ በፊት፣ ራስዎን የፖሊስን ምርመራ ሳያስተጓጉሉ መከላከል እንዲችሉ ፖሊስ ለእርስዎ ወይም ለጠበቃዎ እርስዎ አድርገዋል ብለው ስለሚያስቡት ነገር በቂ መረጃ መስጠት አለባቸው።

- **ምንም ያለመናገር መብት**

ፖሊስ እርስዎ አድርገዋል ብለው ስለሚያስቡት ነገር ለሚጠይቁዎት ማናቸውም ጥያቄዎች መልስ የመስጠት ግዴታ የለብዎትም።

ማንኛውም የሚናገሩት ነገር በጽሁፍ ስለሚቀመጥ ወይም ስለሚቀዳ፣ መዝገብዎ ወደ ፍርድ ቤት ከተወሰደ ፍርድ ቤት በሚቀርቡበት ወቅት እንደ ማስረጃ ሊውል ይችላል።

ፖሊስ ስም፣ አድራሻ፣ የልደት ቀን፣ የትውልድ ቦታ እና የትውልድ ሃገር መረጃዎችን በሚጠይቅዎት ጊዜ መናገር አለብዎት።

- **ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ እንደሆኑ ለጠበቃ መናገር**

ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ እንደሆኑ ለጠበቃ እንዲነገር ፖሊስን መጠየቅ ይችላሉ። ይህም የእርስዎ ጠበቃ፣ ወይም ጠበቃ የማያውቁ ከሆነ፣ ተጠባባቂ ጠበቃ ሊሆን ይችላል። ፖሊስ ጠበቃውን በተቻለ ፍጥነት ለማነጋገር ሁኔታዎችን ያመቻቻል። ይህም ከክፍያ ነጻ ነው።

ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ እንደሆኑ ስለ ደህንነትዎ ለማወቅ ፍላጎት ሊኖረው ለሚችል ሰው መናገር።

ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ እንደሆኑ እንዲያውቁ ለሰዎች እንዲነገር ፖሊስን መጠየቅ ይችላሉ። ቤተሰብዎ ውስጥ ያለው ሰው፣ አጋርዎ፣ ተንከባካቢዎ፣ ጓደኛዎ ወይም የሚያውቁት ሌላ ሰው ሊሆን ይችላሉ። በቻሉት ፍጥነት ለሰዎቹ ይነግሩሎታል።

### ከ16 ዓመት በታች ከሆኑ (ወይም ከ18 ዓመት በታች እና በግዴታ የቁጥጥር ትዕዛዝ ስር ተገዢ ከሆኑ)

- ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ እንደሆኑ ለወላጆችዎ ወይም አሳዳጊዎ ለማሳወቅ መሞከር አለበት።
- ወላጅዎ ወይም አሳዳጊዎ ወደ ፖሊስ ጣቢያ መምጣት እና እርስዎን ማገዝ ይችላሉ።

- **የሚረዳዎት አስተርጓሚ ማግኘት**

እንግሊዘኛ የማይናገሩ ወይም የማይረዱ ከሆነ፣ እርስዎን እንዲረዳዎት ቋንቋዎን የሚናገር ሰው (አስተርጓሚ) እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል። ይህም ነጻ ነው። በፖሊስ ጣቢያ ውስጥ እየተነገረ ያለውን ነገር መገንዘብ መቻልዎ አስፈላጊ ነው።

መስማት የተሳንዎት ከሆኑ ወይም በትክክል መግባባት ላይ ችግር ካለብዎት፣ ፖሊስ የሚረዳዎትን ሰው እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል። ይህም የብሪታኒያ የምልክት ቋንቋ (British Sign Language) አስተርጓሚ ወይም ሌላ ለሁኔታው ተስማሚ ባለሙያ ሊሆን ይችላል። ይህም ነጻ ነው።

- **ብሪታኒያዊ ካልሆኑ**

ብሪታኒያዊ ካልሆኑ፣ የት እንደሆኑ እና በምን ምክንያት ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ እንዳሉ ለመናገር ፖሊስ የእርስዎን ከፍተኛ ኮሚሽን፣ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ እንዲያነጋግራቸው መጠየቅ ይችላሉ። እንዲሁም ለብቻዎ እርስዎን መጎብኘት እና ጠበቃ እንዲያገኝዎት ሁኔታዎችን ማመቻቸት ይችላሉ።

- **ከተከሰሱ ምን ይከሰታል**?

በወንጀል ከተከሰሱ፣ ከፖሊስ እስር ሊለቀቁ ይችላሉ ወይም ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ ሊቆዩ እና በቀጣዩ የስራ ቀን ወደ ፍርድ ቤት ሊወሰዱ ይችላሉ። ወይም የተመደበ ቀን ላይ ወደ ፍርድ ቤት ለመሄድ ከተስማሙ ሊለቀቁ ይችላሉ።

- **ሰነዶችን ማግኘት**

መዝገብዎ ፍርድ ቤት ከቀረበ በመዝገቡ ውስጥ ያለ የማስረጃ ለእርስዎ ወይም ለጠበቃዎ ይሰጣል። ይህም እርስዎ ወይም ጠበቃዎ መከላከያዎን እንዲያዘጋጁ ያስችልዎታል።

እንግሊዘኛ የማይረዱ ከሆነ የጠቃሚ መረጃዎችን ትርጉም የማግኘት መብት አልዎት።

- **የህክምና እርዳታ ማግኘት**

ፖሊስ ስለ ጤናዎ እና ደህንነትዎ ጥያቄዎችን ይጠይቅዎታል። የህክምና ችግር ካለብዎት ወይም መድሃኒት እየወሰዱ ከሆነ ለፖሊስ ማሳወቅ አስፈላጊ ነው። እንዲሁም ማንኛውም ዓይነት የአደንዛዥ ዕጽ ወይም አልኮል ሱስ ካለብዎት ወይም ራስዎን ለመጉዳት የሚያስቡ ከሆነ ለፖሊስ መናገር አስፈላጊ ነው።

ፖሊስ የህክምና ባለሙያ እንዲመረምርዎት ሊጠይቅ ይችላል። ይህ በቁጥጥር ስር እያሉ በአግባቡ ክብካቤ እየተደረገልዎት መሆኑን ለማረጋገጥ ይረዳል። የህክምና ባለሙያ ማግኘት እንዳለብዎት ከተሰማዎት እንግዲያውስ ለፖሊስ ይናገሩ።

የሚያምዎት ከሆነ፣ የህክምና እርዳታ የማግኘት መብት አልዎት።

- **ምግብ እና መጠጥ**

ውሃ በጥያቄዎ መሰረት ይቀርብልዎታል። ከአራት ሰዓት በላይ በቁጥጥር ስር የሚውሉ ከሆነ ምግብ ይሰጥዎታል። ማንኛውም ዓይነት የምግብ ወይም የሃይማኖት መስፈርቶች ካሉ በተቻለ መጠን ቀደም ብለው ለፖሊስ ይናገሩ።

- **ቅሬታ ማቅረብ**

በቁጥጥር ስር ባሉበት ጊዜ ቅሬታ ማቅረብ ከፈለጉ፣ ኢንስፔክተር ወይም ከፍተኛ ማዕረግ ያለውን ሰው ያነጋግሩ። ከእስር ከተለቀቁ በኋላ ቅሬታ ማቅረብ ከፈለጉ፣ ወደ ማንኛውም ፖሊስ ጣቢያ መሄድ ወይም 101 ላይ መደወል ይችላሉ። እንዲሁም የጽሁፍ ፈቃድ እስከሰጧቸው ድረስ፣ ሌሎች ሰዎች እርስዎን ወክለው ቅሬታ እንዲያቀርቡ

ማድረግ ይችላሉ። ወላጅ፣ ጓደኛ፣ አጋራ ወይም የሚያምኑት ሰው ሊሆን ይችላል።

በሚታሰሩበት ጊዜ ወይም በፖሊስ ቁጥጥር ስር እያሉ ጉዳት ወይም አደጋ ከደረሰብዎት ለየስኮትላንድ ፖሊስ ሙያዊ ደረጃዎች መምሪያ Police Scotland Professional Standards Department () ቅሬታ ማቅረብ አለብዎት።

**ተጨማሪ ድጋፍ ከፈለጉ (ይህ መረጃ የአገልግሎት ብቻ እንጂ ስለ መብቶች እንዳልሆነ እባክዎ ልብ ይበሉ):-**

ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ በሚሆኑበት ጊዜ ምን እየተፈጠረ እንዳለ ለመገንዘብ እገዛ ሊያስፈልግዎ ይችላል። ይህ እገዛ ተገቢ አዋቂ (Appropriate Adult) በመባል በሚታወቀው ድጋፍ ሰጪ ግለሰብ ይቀርባል። የአዕምሮ ህመም ወይም የመማር አካል ጉዳት ካለብዎት ይህን እርስዎን ሊመለከት ይችላል። ይህን ድጋፍ እፈልጋለሁ ብለው ካሰቡ ፖሊስን ያነጋግሩ።

ፖሊስ የተገቢ አዋቂ (Appropriate Adult) ድጋፍ ያስፈልግዎታል ብሎ ካሰበ፣ ግለሰቡ እንዲኖር ባይጠይቁም እርስዎ ጋር እንዲሆን ፖሊስ ይጠይቃል።

## 2. በፖሊስ ለሚጠየቁ ግለሰቦች የቀረበ መረጃ

- **እንዲረዳዎት ጠበቃ ማግኘት**

ጠበቃ ማነጋገር የሚፈልጉ ከሆነ ለፖሊስ ይናገሩ። ፖሊስ ጠበቃዎን በተቻለ ፍጥነት ያነጋግርልዎታል።

የጠበቃ ሚና መብቶችዎን እንዲጠበቁ ማድረግ እና ስለ ህጉ ምክር መለገስ ነው።

የሚያውቁትን ጠበቃ ወይም ተጠባባቂ ጠበቃ ለማነጋገር ሊመርጡ ይችላሉ። ይህ ጠበቃ ገለልተኛ ሲሆን ለፖሊስ የሚሰራ አይደለም።

ጠበቃው በነጻ ምክር ሊሰጡዎት እንደሚችል ወይም ምክር ለማግኘት መክፈል ሊኖርብዎት እንደሚችል ይነግርዎታል። ክፍያ መክፈል ካለብዎት፣ ምን ያክል እንደሚያስከፍልዎ እና እንዴት መክፈል እንደሚችሉ ያብራራልዎታል። ፖሊስ ለጠበቃ ክፍያ አይከፍልም ወይም ጠበቃዎ እንዴት ክፍያውን እንደሚያገኝ አይነጋገርም።

በደህንነት ምክንያቶች የተነሳ ጥያቄዎች በአስቸኳይ መጠየቅ ከሌለባቸው በስተቀር ፖሊስ እርስዎን ጥያቄዎች ከመጠየቁ በፊት ከጠበቃዎ ጋር ለብቻዎ እንዲነጋገሩ ይፈቀድልዎታል።

በማንኛውም ሰዓት ጠበቃ የመናገር ሃሳብዎን ሊቀይሩ ይችላሉ። በተቻለ ፍጥነት ለፖሊስ ይናገሩ እና ጠበቃውን ያነጋግሩልዎታል።

ጠበቃው እመጣለሁ ባለበት ሰዓት ወደ ፖሊስ ጣቢያው ካልመጣ፣ ወይም ጠበቃውን እንደገና ማነጋገር ከፈለጉ፣ ፖሊስ ጠበቃውን በድጋሚ እንዲያነጋግረው ይጠይቁ።

በደህንነት ምክንያቶች የተነሳ ጠበቃው ከመገኘቱ በፊት ጥያቄዎች በአስቸኳይ መጠየቅ ከሌለባቸው በስተቀር ፖሊስ እርስዎን ጥያቄዎች በሚጠይቅበት ጊዜ ክፍሉ ውስጥ ጠበቃ እንዲኖር የማድረግ መብቶ አልዎት።

- **ለጥያቄ ምን ያክል ጊዜ ሊታሰሩ ይችላሉ?**

ፖሊስ በወንጀል ክስ ሳይመሰርትብዎት ለ 48 ሰዓታት ለጥያቄ ሊያስርዎት ይችላል። መታሰር ያለብዎት እንደሆነ ለመመልከት በተደጋጋሚ ከፍተኛ ፖሊስ መዝገብዎን መመልከት ይኖርበታል። ይህ ግምገማ ይባላል። ከ 48 ሰዓታ በላይ ሊታሰሩ የሚችሉት ፍርድ ቤት ከፈቀደ ብቻ ነው። ፍርድ ቤት ያለ ምንም ክስ የእስር ጊዜዎን ከታሰሩበት ቀን እስከ 14 ቀን ድረስ ሊያራዝም ይችላል። በእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ የሚከተሉት ሊሰጥዎት ይገባል:-

- ○ እስርዎን ለማራዘም ማመልከቻ የቀረበበት የጽሁፍ ሰነድ፤
- ○ ማመልከቻው የቀረበበት ሰዓት፤
- ○ ማመልከቻው ፍርድ ቤት ውስጥ ችሎት የሚቀርብበት ሰዓት፤ እና
- ○ ተጨማሪ እስር ያስፈለገበት ምክንያት(ቶች)።

እስርዎን ለማራዘም እንዲሁም በተጨማሪ ለማራዘም ማመልከቻ በሚቀርብበት በእያንዳንዱ ጊዜ ማሳወቂያ ለእርስዎ (እና ህጋዊ ተወካይዎ) መሰጠት አለበት።

አሞቺ የሆነ ሁኔታ ውስጥ ካልሆኑ በቀር፣ እርስዎ እና ጠበቃዎ ስለ ውሳኔው ሃሳብ የመስጠት መብት አላችሁ። ጠበቃው ስለዚህ ምክር ሊሰጥዎ ይችላል።

- **ገለልተኛ የእስር ቤት ጉብኚዎች** (Independent Custody Visitors)

ፖሊስ ጣቢያዎች ውስጥ መግባት የሚፈቀድላቸው የማህበረሰቡ አባላት አሉ። ገለልተኛ የእስር ቤት ጉብኚዎች በመባል የሚታወቁ ሲሆን የታሰሩ ሰዎች በስርዓት እየተስተናገዱ እንደሆነ እና መብቶቻቸውን እያገኙ እንደሆነ ለማረጋገጥ በበጎ ፈቃደኝነት ይሰራሉ።

ገለልተኛ የእስር ቤት ጉብኚን የማግኘት ወይም እንዲገበኙዎት የመጠየቅ መብት የልዎትም ነገር ግን ጎብኚው እርስዎን ለማግኘት ሊጠይቅ ይችላል። ገለልተኛ የእስር ቤት ጉብኚው በቁጥጥር ስር እያሉ ከጎበኙዎት ደህንነትዎ እና መብቶችዎ እንደተከበሩ ለማጣራት ከፖሊስ ገለልተኛ ሆነው ይሰራሉ። እነርሱን ለማነጋገር መፈለግ የእርስዎ ምርጫ ነው።